በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS

የፕሬስ መግለጫ PRESS RELEASE

# የተከበሩ አባዱላ ገመዳ የክብር ዶክትሬት ተቀበሉ

የኢፌዲሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተከበሩ አባዱላ ገመዳ ከደቡብ ኮሪያው የሐንዶንግ ግሎባል ዩኒቨርሲቲ የህግ የክብር ዶክትሬት ተቀብለዋል፡፡

ለተከበሩ አባዱላ ገመዳ የክብር ዶክትሬቱ የተሰጣቸው፣ ወታደራዊውን የደርግ ስራዊት ለመደምሰስ በተደረገው የትጥቅ ትግል ከመሳተፍ ጀምሮ በተለያዩ የአገሪቱ ከፍተኛ የሃላፊነት ቦታዎች ላይ በተለያም በኢትዮጵያ የመከላከያ ሚኒስትርነት፣ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝዳንትነት፣ እንዲሁም አሁን የኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ በመሆን ለአገራቸው ሰላም ዴሞክራሲና ልማት የበኩላቸውን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ለረጅም ጊዜያት ያበረከቱ በመሆናቸው መሆኑን የዩንቨርስቲው ፕሬዝዳንት Dr.Soon Heung Chang ገልጸዋል፡፡

በስነ-ስርዓቱ ላይ የተከበሩ አባዱላ ገመዳ ዩኒቨርሲቲው ለሰጣቸው እውቅና አመስግነው፣ የተሰጣቸው እውቅና የራሳቸው ብቻ ሳይሆን በረዥሙ የትጥቅ ትግል እና ከዚያ በኃላ ባለፉት ሃያ አምስት አመታት በአገራችን ዘርፈ ብዙ ለውጥ ለማምጣት ለታገሉና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት የተሰጠ እውቅና እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

በዩኒቨርስቲው ደረጃ ከአገሪቱ ዜጋ ውጭ ህዝባዊ አገልግሎት ለሰጡ ግለሰብ የክብር ዶክትሬት ሲሰጥ ለመጀመሪያ ጊዜ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በስነ-ስርዓቱ ላይ በዩኒቨርሲቲው በመማር ላይ ያሉት ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ከሌሎች የአፍሪካ ተማሪዎች ጋር የተለያዩ ባህላዊ ውዝዋዜዎችን በማቅረብ ለእውቅና አሰጣጡ ያላቸውን አድናቆት ገልጸዋል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ የደቡብ ኮሪያ የወቅቱና የቀድሞ የምክር ቤት አባላት ህብረት ባዘጋጁት የእራት ግብዣ ላይ፣ የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ለደቡብ ኮሪያ ህዝብ ያደረገውን ውለታ መነሻ በማድረግ ለአፈ ጉባኤ አባዱላ ገመዳ ሜዳልያ አበርክተዋል፡፡

*የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር*

*ቃልአቀባይ ጽ/ቤት*

*መስከረም 20 ቀን 2009 ዓ.ም*

P.O.BOX 393 TEL: 011 5 517345 FAX: 011 5 514300 E-mail: mfa.press@ethionet.et Website: www.mfa.gov.et